# በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የውጭ ዜጎች ወሳኝ ኩነት ምዝገባ
# አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 5/2009

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የውጭ ዜጎች ወሳኝ ኩነት ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 5/2009" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **አውጪው አካል**

   የፌደራል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ በወሳኝ ኩነት ምዝገባና የብሄራዊ መታወቂያ አዋጅ ቁጥር 760/2004 አንቀጽ 69(2) በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

3. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1. **"የውጭ አገር ሰው "** ማለት የኢትዮጵያ ዜጋ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ነው፡፡
   2. **"የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆነ የውጭ ዜጋ"** ማለት የሌላ ሀገር ዜግነት ከመያዙ አስቀድሞ የኢትዮጵያ ዜግነት የነበረው ወይም ከወላጆቹ፣ ከአያቶቹ ወይም ከቅድመ አያቶቹ ቢያንስ አንዱ በማናቸውም ጊዜ የኢትዮጵያ ዜግነት ይዞ የነበረ የውጭ ዜጋ ሲሆን፣ የኢትዮጵያን ዜግነት በመተው የኤርትራ ዜግነትን መርጦ የያዘ ሰውን አይጨምርም፡፡
   3. **"የመኖሪያ ፈቃድ"** ማለት ወደ ኢትዮጵያ ለመኖር ለሚገቡ እና ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖሩ ለተፈቀደላቸው ለውጭ አገር ዜጎች ወይም ለኤርትራዊያን ለአንድ ዓመት የሚያገለግል መታወቂያ ነው፡፡
   4. **"ቪዛ"** ማለት ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቆይ እና እንዲገባ የሚሰጥ ማስረጃ ነው፡፡

5. "የኢትዮጵያ ተወላጅ መታወቂያ ካርድ" ማለት ለኢትዮጵያ ተወላጅ ለሆነ የውጭ አገር ዜጋ ወይም በልዩ ሁኔታ ለፈቀደላቸው የሚሰጥ መታወቂያ ካርድ ነው፡፡
6. በአዋጅ ቁጥር 760/2004፣ 1049/2009 እና መመሪያ ቁጥር 2/2008 እና 3/2008 ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች በዚህ መመሪያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የውጭ አገር ዜጎች ላይ የሚከሰት የወሳኝ ኩነት ምዝገባን በተመለከተ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም የስደተኞች ወሳኝ ኩነት ምዝገባን አይጨምርም፡፡

## 5. መዝጋቢ አካላት

1. ከትውልደ ኢትዮጵያዊያን ውጪ በሆኑ የውጭ አገር ዜጎች ላይ የሚከሰት ወሳኝ ኩነት ምዝገባ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እያንዳንዱ ክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ባለበት ወረዳ ምዝገባው ይከናወናል፡፡
2. ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የሆኑ የውጭ ዜጎች ወሳኝ ኩነት ምዝገባ በሁሉም ክልልና ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ዝቅተኛ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ይከናወናል፡፡

## 6. የፓስፖርት ደጋፊ ማስረጃነት በተመለከተ

ፓስፖርት ደጋፊ ማስረጃ ሆኖ ለውጭ ዜጋ ሲቀርብ ጊዜው ያላለፈ ቪዛ ጋር ተያይዞ መቅረብ ያለበት ሆኖ ለጅቡቲ እና ለኬኒያ ዜጋ ግን ቪዛ ሳያስፈልግ ፓስፖርት ብቻ ማቅረብ በቂ ነው፡፡

## 7. ከውጭ አገር የሚገቡ ሰነዶችን በተመለከተ

ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የኩነት ምዝገባ ደጋፊ ሰነዶች በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካልተረጋገጠ እና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ኤጀንሲ ካልተመዘገበ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Vital Events Registration Agency

8. **የምዝገባ ጊዜን በተመለከተ**

በማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ (ትውልደ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ) ላይ የሚከሰት ወሳኝ ኩነት የምዝገባ ጊዜ ገደብ በመመሪያ ቁጥር 2/2008 መሰረት ምዝገባው የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

9. **ክልከላ**

በአንድ የውጭ ዜጋና በአንድ ስደተኛ መካከል የሚከሰተ ኩነትን(ልደት፣ ጋብቻ፣ ፍቺ እና ሞት) መመዝገብ የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የልደት ምዝገባ ቦታ፣ ቅድመ ሁኔታዎችና ደጋፊ ማስረጃዎች

9. **የልደት ምዝገባ ቦታ፡-**

9.1. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የውጭ ዜጎች የልደት ምዝገባ ቦታ በአዲስ አበባ ከተማ አስሩ ክፍለ ከተሞች በሚገኙበት ወረዳ ምዝገባው የሚከናወን ይሆናል፡፡

9.2. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የውጭ ዜጎች የልደት ምዝገባ ቦታ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሆኖ ከዚህ በታች ከ "ሀ" እስከ "ሐ" በተጠቀሰው መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

ሀ. የልደት ምዝገባ ቦታ በአስመዝጋቢው መደበኛ መኖሪያ ቦታ ወይም ልደቱ በተከሰተበት አቅራቢያ በሚገኝ የአስተዳደር ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡

ለ. ልደቱ የተከሰተው በጎዳና ተዳዳሪ ከሆነ ልደቱ በተከሰተበት አቅራቢያ በሚገኝ የአስተዳደር ጽህፈት ቤት ይመዘገባል፡፡

ሐ. ልደቱ የተከሰተው በጋራ መኖሪያ ስፍራ ከሆነ በአቅራቢያው በሚገኝ የአስተዳደር ጽህፈት ቤት ይመዘገባል፡፡

10. **ቅድመ ሁኔታዎች (ለትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ እና ላልሆኑ የውጭ ዜጎች) :-**

1. **የልደት አስመዝጋቢዎች**

ሀ. የህፃኑ ወላጆች በህይወት ካሉ አባት እና እናት ሁለቱ፣

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Vital Events Registration Agency
The Federal Democratic Republic of Ethiopia Vital Events Registration Agency

ለ. ከወላጆቹ አንዱ በአካል ተገኝተው ማስመዝገብ ካልቻሉ አባት ለእናት ወይም እናት ለአባት ልዩ ውክልና በመስጠት ማስመዝገብ አለበት፡፡

ሐ. ከሁለቱ አንዱ በህይወት የሌሉ እንደሆነ በህይወት ያለው ማስመዝገብ አለበት፤

መ. ሁለቱም ወላጆች በህይወት የሌሉ ከሆነ የህፃኑ አሳዳሪ ወይም ህጋዊ ሞግዚት ወይም ህፃኑን በመንከባከብ ላይ ያለ አካል ማስመዝገብ ይችላል፡፡

**11. ደጋፊ ማስረጃዎች (ለትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ እና ላልሆኑ የውጭ ዜጎች)**

1. አስመዝጋቢው ጊዜው ያላለፈበት የነዋሪነት/ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት እና ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊነት መታወቂያ መቅረብ አለበት፡፡
2. የልደት ማሳወቂያ ቅጽ ከጤና ተቋም መቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም ይህ መመሪያ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ለተከሰተ ልደት የማሳወቂያ ቅጽ ማቅረብ አስገዳጅ አይደለም፡፡
3. የህጻኑ አሳዳሪ ወይም ሕጋዊ ሞግዚት ልደቱን ለማስመዝገብ ሲቀርብ ከፍርድ ቤት የተሰጠ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. ዘግይተውና የምዝገባ ጊዜውን አሳልፈው ለሚቀርቡ ተመዝጋቢዎች የዘገዩበትን ወይም ጊዜ ያሳለፉበትን ማስረጃ በማቅረብ መመዝገብ ይችላሉ፡፡

**12. የክብር መዝገቦችና የምስክር ወረቀት አመዘጋገብ በተመለከተ**

የክብር መዝገቦችና ምስክር ወረቀቶችን በተመለከተ ከዚህ በፊት ለኢትዮጵያዊያን ወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና ምስክር ወረቀት አገልግሎት በተዘጋጀው መሰረት ይፈፀማል፡፡ ተመዝጋቢውን ወይም አስመዝጋቢውን የማይመለከቱ ጉዳዮች ሳይሞላ ወይም ሳይመዘገብ በሰረዝ የሚታለፉ ይሆናል፡፡

**13. "ዜግነት"፣ "የትውልድ ወር፣ ቀንና ዓመት ምህረት" እና "የትውልድ ቦታ/ሀገር"**

ዜግነት ፣የትውልድ ወር ቀንና ዓመት ምህረት እና የትውልድ ቦታ/ሀገር ተመዝጋቢው ወይም አስመዝጋቢው የውጭ ዜጋ ከሆነ ከፓስፖርት ወይም ከትውልደ ኢትዮጵያዊነት መታወቂያ ወይም ከመኖሪያ ፈቃድ ላይ በመውስድ ይመዘገባል፡፡

## ክፍል ሶስት

## በጋብቻ ምዝገባ ወቅት መሟላት የሚገባቸው

## ቅድመ ሁኔታዎችና ደጋፊ ማስረጃዎች

### 14. የጋብቻ ምዝገባ የሚካሄድበት ቦታ

1. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የውጭ ዜጎች የጋብቻ ምዝገባ ቦታ በአዲስ አበባ ከተማ አስሩ ክፍለ ከተሞች በሚገኙበት ወረዳ ምዝገባው የሚከናወን ይሆናል፡፡
2. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የውጭ ዜጎች የጋብቻ ምዝገባ ቦታ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሆኖ ተጋቢዎች በጋራ ለመኖር የሚወስኑት ቦታ ይሆናል፡፡

ተጋቢዎች በጋራ የሚወስኑት ቦታ ማለት፡-

1. ከተጋቢዎች አንዱ ይኖርበት በነበረው መደበኛ መኖሪያ ቦታ
2. ከተጋቢዎች በአንደኛው ወላጆች መደበኛ መኖሪያ ቦታ
3. ከተጋቢዎች በአንደኛው የቅርብ ዘመዶች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ማለት ነው፡፡

### 15. ቅድመ ሁኔታዎች (ለትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ እና ላልሆኑ የውጭ ዜጎች)

1. ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈፀም ማሰባቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን ለመፈፀም ከወሰኑበት ሃያ/20/ ቀን በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማስታወቅ አለባቸው፡፡
2. የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄው በቀረበለት ቀን ከተጋቢዎቹ ጋር በመነጋገር ከወሰነ በኋላ በማግስቱ ጋብቻው የሚፈፀምበትን ቀን በመግለጽ አመቺ በሆነ ቦታ ወይም መንገድ ለ15 ተከታታይ ቀን የሚቆይ ማስታወቂያ ያወጣል፡፡
3. ማስታወቂያ ከተለጠፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት ተከታታይ 10 ቀናት ውስጥ የጋብቻ [illegible]ሚያ በጽሁፍ መቅረብ አለበት፤ መቃወሚያ ሊያቀርቡ የሚችሉ ወላጆችና

Federal Democratic Republic of Ethiopia Vital Events Registration Agency

ተወላጆች፣ አቃቤ ሕግ፣ አሳዳሪ ወይም የቀደመ ጋብቻ አለኝ የሚል ሰው መሆን አለበት፡፡

4. የክብር መዝገብ ሹሙ በቀረበው የጋብቻ መቃወሚያ ላይ በአምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ውሳኔ በመስጠት ማሳወቅ አለበት፡፡
5. ወንዱም ሆነ ሴቷ 18 /አስራ ስምንት/ ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ መፈጸም አይችሉም፡፡
6. ጋብቻ ህግ በሚከለክላቸው የስጋና የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡
7. የጋብቻ ምዝገባ የሚፈፀመው በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል የተፈፀመ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ (በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የተፈፀመ መሆን አለበት ማለት ነው)፡፡
8. ተጋቢዎች በፍርድ ቤት እንዳያጋቡ የተከለከሉ መሆናቸውን የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ የተገኘ እንደሆነ የክብር መዝገብ ሹሙ ጋብቻውን አይመዘገብም፡፡
9. አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኃላ አንድ መቶ ሰማኒያ ቀን ማለፉ ካልተረጋገጠ በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡ ሆኖም ግን የወለደች እንደሆነ ወይም ከቀድሞ ባሏ ጋር ጋብቻ የምትፈፅም ከሆነ ወይም ነፍሰ-ጡር አለመሆኗ በህክምና ከተረጋገጠ ወይም በብቸኝነት እንዳትኖር ፍርድ ቤት የፈቀደ መሆኑ ሲረጋገጥ ጋብቻው ይመዘገባል፡፡
10. የሚፀና ጋብቻ ተፈፀመ የሚባለው ተጋቢዎቹ ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው፡፡
11. በሙሽራው በኩል 2 በሙሽሪት በኩል 2 በድምሩ 4 ምስክሮች መቅረብ አለባቸው፡፡
12. ማንኛዉም የውጭ ዜጋ /ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ዜጋን ጨምሮ/ የክልሉ ቤተሰብ ህግ ካልፈቀደ በስተቀር አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ ይሄዉ ጋብቻ ፀንቶ በቆየበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ መፈጸም አይችልም፡፡

## 16. ደጋፊ ማስረጃዎች (ለትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ እና ላልሆኑ የውጭ ዜጎች)

1. ተጋቢዎች ጊዜው ያላለፈበት የነዋሪነት/ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት እና ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊነት መታወቂያ መቅረብ አለበት፡፡
2. የተጋቢ ምስክሮች አገልግሎቱ ያላለፈበት የነዋሪነት/ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት መቅረብ አለበት፡፡
3. ሙሽራው/ዋ ከዚህ በፊት ያገባ/ች የፈታ/ች ከሆነ የፍች ምስክር ወረቀት መቅረብ አለበት/ባት፡፡

4. ተጋቢው/ዋ የቀድሞ ጋብቻ በሞት የተለያዩ ከሆነ የሞት ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት/ባት፡፡
5. አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ አዲስ ጋብቻ መፈፀም ብትፈልግ አንድ መቶ ሰማኒያ ቀን ሳይሞላ ለማግባት የሚያስችላት ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ አለባት፡፡
6. ከ 6 ወር ወዲህ የተነሱት እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት መጠኑ 3 በ 4 ተመሳሳይ የሆነ የተጋቢዎች ፎቶ-ግራፍ መቅረብ አለበት፡፡
7. በሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ስርዓት የተፈፀመ ጋብቻ የተጋቢዎች 4 /አራት/ ምስክሮች ወይም በጋብቻ ስርዓቱ ላይ የታደመ ሰው በክብር መዝገብ ሹሙ ፊት በአካል ቀርበው ፊርማቸውን ማኖር አለባቸው፡፡
8. ዘግይተውና የምዝገባ ጊዜውን አሳልፈው ለሚቀርቡ ተመዝጋቢዎች የዘገዩበትን ወይም ጊዜ ያሳለፉበትን ማስረጃ በማቅረብ መመዝገብ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አራት

## የፍቺ ምዝገባ ቦታ፣ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ደጋፊ ማስረጃዎች

17. የፍቺ ምዝገባ ቦታ

17.1. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የውጭ ዜጎች የፍቺ ምዝገባ ቦታ በአዲስ አበባ ከተማ አስሩ ክፍለ ከተሞች በሚገኙበት ወረዳ ምዝገባው የሚከናወን ይሆናል፡፡

17.2. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የውጭ ዜጎች የፍቺ ምዝገባ ቦታ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሆኖ፤

1. ተፋቺዎች በተለያዩ መደበኛ መኖሪያ ቦታ የሚኖሩ ከሆነ ዉሳኔ በተሰጠበት አቅራቢያ በሚገኝ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ይሆናል፡፡
2. ተፋቺዎች በፍቺ ወቅት አብረው የሚኖሩ ከሆነ የሁለቱ የጋራ መደበኛ መኖሪያ በሚገኝበት አስተዳደር ጽሕፈት ይሆናል፡፡

18. ቅድመ ሁኔታዎች

1. ፍቺው በተፋቺዎቹ የጋራ ወይም ከተፋቺዎች በአንዱ መደበኛ መኖሪያ ቦታ በሚገኝ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተፈጸመ መሆን አለበት፣
2. የፍቺ አስመዝጋቢ ሆነው የሚቀርቡት ተፋቺዎች በጋራ ወይም ከተፋቺዎች አንዱ ወይም የተፋቺዎች ህጋዊ ወኪል መሆን አለበት፣

19. ደጋፊ ማስረጃዎች (ለትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ እና ላልሆኑ የውጭ ዜጎች)

1. ፍቺው ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት የተከናወነ መሆኑን የሚገልፅ ውሳኔ ግልባጭ መቅረብ አለበት።
2. ተፋቺዎች ፍቺውን ለማስመዝገብ ሲመጡ ጊዜው ያላለፈበት የነዋሪነት/ብሄራዊ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት እና ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊነት መታወቂያ መቅረብ አለበት።
3. ፍቺው የሚመዘገበው በወኪል ከሆነ ልዩ ውክልና ማስረጃ መቅረብ አለበት።
4. በዚህ መመሪያ መሰረት የጋብቻ ምስክር ወረቀት ቀደም ስል የተሰጠ እንደሆነ መቅረብ አለበት፣
5. ዘግይተውና የምዝገባ ጊዜውን አሳልፈው ለሚቀርቡ ተመዝጋቢዎች የዘገዩበትን ወይም ጊዜ ያሳለፉበትን ማስረጃ በማቅረብ መመዝገብ ይችላሉ።

## ክፍል አምስት

## የሞት ምዝገባ ቦታ፣ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ደጋፊ ማስረጃዎች

20. የምዝገባ ቦታ

20.1. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ የውጭ ዜጎች የሞት ምዝገባ ቦታ በአዲስ አበባ ከተማ አስሩ ክፍለ ከተሞች በሚገኙበት ወረዳ ምዝገባው የሚከናወን ይሆናል።

20.2. ትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የውጭ ዜጎች የሞት ምዝገባ ቦታ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሆኖ፤

1. የሞት ምዝገባ ቦታ በሟች መደበኛ መኖሪያ ቦታ ወይም ሞቱ በተከሰተበት አቅራቢያ ባለው የአስተዳደር ጽህፈት ቤት ይሆናል።

2. ማንነቱ ወይም መደበኛ መኖሪያ ቦታው ለማይታወቅ ሟች የሞት ምዝገባ ቦታ አስከሬኑ በተገኘበት ቦታ አቅራቢያ የሚገኝ የአስተዳደር ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡
3. ሞቱ የተከሰተው በጋራ መኖሪያ ስፍራ የሆነ እንደሆነ የሞት ምዝገባ ቦታ አቅራቢያ በሚገኝ የአስተዳደር ጽህፈት ቤት ይሆናል፡፡

## 21. ቅድመ ሁኔታዎች (ለትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ እና ላልሆኑ የውጭ ዜጎች)

1. ከሟች ጋር አብሮ ይኖር የነበረ ሰው፣ አብሮ ይኖር የነበረ ሰው የሌለ እንደሆነ የሟች የስጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች፣ እነዚህ የሌሉ እንደሆነ የቅርብ ጎረቤት ወይም ስለሟቹ መሞት የሚያውቅ ማንኛውም ሰው ሟች መሞቱን ማስመዝገብ አለበት፡፡
2. ሞቱ የተከሰተው በጋራ መኖሪያ ስፍራ ከሆነ የተቋሙ ሃላፊ ሞቱን ለማስመዝግብ መቅረብ አለበት፡፡
3. በአደጋ ምክንያት ከሞቱ ሰዎችና አደጋው ከደረሰባቸው ተጎጂዎች ጋር አብሮ የነበረ ሰው ሊገኝ አለመቻሉን ካጣራ አካል የተሰጠ ማስረጃ ሲቀርብ ሞቱ ይመዘገባል፡፡

## 22. ደጋፊ ማስረጃዎች (ለትውልደ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ እና ላልሆኑ የውጭ ዜጎች)

1. የሞት ማሳወቂያ ቅጽ ከጤና ተቋም መቅረብ አለበት፡፡
2. የሟች ፓስፖርት እና ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊነት መታወቂያ መቅረብ አለበት፡፡
3. ሞቱን የሚያስመዘግበው ፖሊስ ከሆነ ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ/ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡
4. ሞቱ የሚመዘገበው በግለሰቡ መጥፋት ውሳኔ ምክንያት ከሆነ የመጥፋት ውሳኔ ግልባጭ ከፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡
5. ዘግይተውና የምዝገባ ጊዜውን አሳልፈው ለሚቀርቡ ተመዝጋቢዎች የዘገዩበትን ወይም ጊዜ ያሳለፉበትን ማስረጃ በማቅረብ መመዝገብ ይችላሉ፡፡

## ክፍል ስድስት

## የተለያዩ ድንጋጌዎች

### 23. የክብር መዝገብ እና የምስክር ወረቀት መረጃዎች ስለማረም፣

የክብር መዝገብና የምስክር ወረቀት እርማት በመመሪያ ቁጥር 2/2008 መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

### 24. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ

በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና መረጃ አደረጃጀት፣ ቅብብሎሽ፣ አያያዝና አቅርቦት አፈፃፀም በመመሪያ ቁጥር 2/2008 እና 3/2008 መሰረት የሚፈፀሙ ይሆናሉ፡፡

### 25. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 3/2009 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ 5 ቀን 2009 ዓ.ም

ኤልሳ ተስፋይ

የፌዴራል ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ

ዋና ዳይሬክተር